# ይድረስ ለጀርመን ድምፅ

## ቦን

በሳምንታዊው ራዲዮ ዝግጅት የአጤ ኃይለ ሥላሴን የምዕራብ ጀርመን ጉብኝት ከዛሬ 60 ዓመታት በፊት ትውስታ በተመለከተ እ.አ 9/1½0014 የተደረገውን ውይይት ይመለከታል።
የውይይቱ ተካፋይ ከነበሩት አቶ ይልማ ኃይለ ሚካኤል ከበርሊን ከተማ ነዋሪ እንዲሁም ዶክተር ጌጤ የተባለው ከሃምቡርግ ዩኒቩርስቲ የእሲያ አፍሪቃ ዘርፍ ያማርኛ አስተማሪና ሌላ ሁለት ጀርመኖች በአስተርጓሚ በጀርመንና በእንግሊዘኛ ቋንቋ ተቀነጭቦ ያቀረበውን በአጽንኦት ሰምተነዋል። በመሆኑም ግንዛቤያችንን ቀጥሎ ለማቅረብ ግድ ብሏል።

፩ኛ ጋዜጠኛው አቶ ይልማ በአጠቃላዩ ያቀረቡትን ትንታኔና ድምዳሜ ላይ እንስማምለን። ሐቁን በትክክል በማስቀመጣቸው ላቅ ያለ ምስጋና ባሉበት ይድረሳችው እንላለን።

፪ኛ ልሂቅ ተብይው የሃምቡርግ ዩኒቨርስቲ ያማርኛ አስተማሪ ዶክተር ጌጤ ግን ሲዘላብድ ነበር። ፍጹም ቱሪማንቱሪ ልፊፋው እጅግ በጣም ያሳፍራል። ስለምን ብለችሁ ለምትጠይቁት ሁሉ እጅግ በቂ ምላሽ እንሰጣችኋለን። በጥልቅና በስፋት ለማገናዘብ በማንኛው ጊዜና ስፍራ ዝግጁዎች ነን። የሀንቡርጉ ምሁር ተብየው ተራ ጥሩንባ ነፊ በመሆን በበላባት ይጮሃል። በጀርመን መንግሥትና ኢትዮጵያ መካከል ግንኙነት ከተፈጠረ 500 ዓመት ሆኖታል በማለት አነብንቧል። እረ! እንዴት ሆኖ ነው? አምስት መቶ ዓመታት የሚሆነው ብለን ለመጠይቅ ግድ ይላል። ጀርመን ማዕከላዊ መንግሥት የመሠረተችው እኮ ከዳግማዊ አጤ ቴዎድሮስ መቅደላ ሞት 3 ዓመታት በኋላ ነው።

፫ኛ ኢዩብ ሉዶልፍ የተባለው አንድ ግለስብ እ.አ (1624-1704) የሴማው ቋንቋዎችና የሕግ ተማሪ የነበረ በስውዲን ንግሥት ተላላኪነት ወደ ሮም ከተማ ተልኮ በዚያም ከሚገኙት መዛግብት ለታሪኳ ሰነድ እንዲፈልግላት በሄደበት ወቅት በአጋጣሚ ከኢትዮጵያዊው ካቶሊካዊ የአጤ ሱስንዮስ አማካሪ ከነበረው አባ ጎርጎሪዎስ የመካነ ሰላም (ቤተ ዐምሐራ) ተወላጅ ስደተኛ ጋራ ተዋውቆ ግእዝንና አማርኛ ተምሮ ሰለ ኢትዮጵያ ታሪክና ቋንቋዎች በአውሮፓ ከነ ፍራንኮ አልቫሬስ በኋላ መጻሕፍትን አሳትሟል። አባ ጎርጎሪዎስንም ከሮም በሳክሰን-ጎታው መስፍን ተባባሪነት ጋብዘውት ለጥቂት ወራት ያህል ቆይቶ ወደ ኢትዮጵያ ተመልሶ በሳክሶን ጎታው መስፍን የበላይ ጠባቂነት ለመሥራት ታቅዶ በጉዞው ላይ መርከብ ተገልብጦ ምሥራቅ ሜድትራኒያን ባሕር ውስጥ ሰምጦ ቀረ። በውይይቱ የጀርመን መንግሥትና ኢትዮጵያ ግንኙነት ከ500 ዓመታት በላይ ተብሎ የተለፈፈው ተራ ውሸት የሚሆነው የዛሬይቱ ጀርመን ማዕከላዊ መንግሥት የመሠረተችው በ19ኛው ክፍለ ዘመን በታላቁ የፕራሻያ መሪ ቢስማርክ እ.አ በ1871 ዓ.ም ስለሆነ ነው። ከሁሉም በላይ ሐቁ የጀርመንኛ ቋንቋ ዘዬ ተናጋሪ አያሌ መሳፍንት ለምሳሌ የባየር.፣ የሳክሶን ጎታ፣ የቩተምበርግ፣ የባደን፣ የፕራሻያ፣ የፋልዝ፣ የሃንቡርግ፣ የጎታ ወዘተረፈ አካባቢዎች በርካታ መሳፍንት ሁሉ በያለበት በሥልጣን ይቅርና በጠላ ግብር ገብር አልገብርም እንኳ ሳይቀር ዘወትር እርስ በርሳቸው ሲዋጉና ሲጨራረሱ እንደነበር በግልጽ ይታወቃል። ለማያውቁሽ ታጠኚ ይላል ያገራችን አዋቂ ሰው! በመሆኑም በከንቱ መቀባጠር ምን ይሉታል!!

፬ኛ ጀርመንኛ ተናጋሪ ግለሰቦች ለእንግሊዝ ቅኝገዥዎችና ተስፋፊዎች ቅጥረኛ በመሆን ብቻ በተለይም የፕሮቴስታንት ክርስቲያን ተብዬ ወንጌል ሰባኪያውያን የተባሉት የቀበሮ ባሕታውያን ሁሉ እንደ ዩሐን ክራፍ የቩተምበርግ የጀርመን ተወላጅ፣ ጎባት፣ ኩግለር፣ ኢዘንበርግ፤ ወዘተረፈ የመሳሰሉት ቅጥረኞች በምድረ ግብፅ በኩል አድርገው ኢትዮጵያ በመግባት በአፍሪቃ አህጉር የኦርቶዶክስ ተህዋህዶ ክርስትና ሃይማኖትን ለማስለወጥ የተደረገውን ቀቢፀ ተሰፋ፣ ፍጹም

የለየለት ፀረ አበሻ ዘመቻና ሴራ ስለምን በተዋዋዩቱ ዘንድ አልተጠቀሰም? ይልቁንም ዛሬስ ቢሆን የጀርመን መንግሥትና ድርጅቶች ሁሉ የጎሳ ፖለቲካንና የባንቱስታን አፓርታይድ የኢትዩጵያ ሕዝብን በዘርና ቋንቋ ከፋፍሎ በመግዛት ኢትዩጵያን ከዓለም ካርታ ላይ ልክ እንደ ዩጎዝላቢያ ለመፋቅ ወያኔና ሻዕቢያን እንዲሁም ኦነግና ሌሎቹን ፀረ ኢትዩጵያ ወገኖችን ሁሉ በኢኮኖሚና ፖለቲካው መስክ ከፍተኛ ድጋፍ ሰጭ ከሆኑት የምዕራብ ሀገራት በግንባር ቀደም ደረጃ መገኘታቸው የተረጋገጠ መሆኑ ለምን ይሸፈጣል? የእንግሊዝ ክርስቲያን ሚሲዎን ማኅበር ቅጥርኛ የነበሩት ብዙ የጀርመን፣ የስዊድንና የስዊዘርላንድ ፕሮቴስታንት ተብዬ አወናባጅ ሰላይዎች ሁሉም ተባብረው በአፍሪቃ ብቸኛ የጥቁር ሕዝብ ነፃ መንግሥትና የኢትዩጵያ ኦርቶዶክስ ሃማኖትን ከግብፅ እስላማዊ ተስፋፊው ባሪያ ፈንጋይና ነጋዴው የእስማኤል ፓሻ መንግሥት ጋራ ወግነው የወረራው ዘመቻ መሪና አስተባባሪ በመሆን እነ የሓን ክራፍ፣ ሙዝንጅር፣ ወዘተ. በኢትዩጵያ ነጻ ሀገራዊነት ላይ ሲያቀናቡሩት የነበረው ሴራ ከቶ መቸም አይዘነጋም።

፫ኛ የኢትዩጵያ መንግሥት ከጀርመን መንግሥት ጋር ዲፕሎማቲካዊ ግንኙነት የመሠረተው ከዳግማዊ አጤ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት ወዲህ ነው። እርግጥ ነው አለቃ ታዬ ገብረ ማርያም በብርሊን የግእዝና ዐማርኛ ቋንቋ እንዲያስተምሩ በተጠይቀው መሠረት አጤ ምኒልክ ልከዋቸው መጥተው ነበር። ሚትቮሕ ከተባለው ይሁዲ ጋራ ለሦስት ዓመት ያህል በሠሩም እንኳ ጥሩ ግንኙነትና ትብብር ግን አልነበራቸውም። ወደ አገራቸው ሲመለሱ ከጀርመን መንግሥት አንዲትም ሽልማት አልተሰጣቸውም። ታዲያ በውይይቱ አቶ ጌጤ ተሸልምው ተመለሱ ያለው አንድም የራሱ ፈጠራ ትረካ ሁለትም ሰምቶ ያለ ማስረጃ የሚያራግበው ነው። ይልቅስ አለቃ ታዬ ሽልማት ያገኙት ከጣሊያን መንግሥት እንደሆነ የብርሊን ነፃ ዩኒቨርስቲ የታሪክና ሴማዊ ቋንቋዎች የግዝና ዐማርኛ አስተማሪው ፕሮፌስረ ራይነር ቮግትስ ያደረጉት ጥናት በትክክል ያስረዳል። የጀርመን ይሁዲ ሴማዊ ተብየው ሚትቮኽ እጣ ፋንታ ደግሞ የጀርመን አውሬ ናዚዎች "አሪያንነት" እሳቤና ምርጥ ዘር ፕሮፓጋንዳ ሲሰፍን ሰለባ ሆኖ ወደ እንግሊዝ ፈጥኖ በመሰደድ ሕይወቱን ማትረፉ ይታወቃል።

በሌላ በኩል ደግሞ የኢትዩጵያ መንግሥትና ሕዝብ ከጣሊያን ክልስ ክልስልስ ማለትም ግማሻ ሻንቅላዎች ቅልቅል ወገን ከሆነው የጥንቱ ሮማውያን አረመኔዎች ውላጅ ጣሊያን ተብየ አሃዳዊ መንግሥት ልክ እንደ ጀርመን በቅርቡ ከመሠረተ በኋላ በእንግሊዝ ርዳታና ድጋፍው በአፍሪቃ ቀንድና ቀይ ባሕር ዳርቻ ቅኝ ግዛት መሥርቶ በመስፋፋት ኢትዩጵያን በመላው ለመያዝ ተመኝቶ የጦር ወረራ በአደረገበት ወቅት የአረማውያን አውሬዎቹ የጀርመን መንግሥት ከጣሊያን ድቅል ወገናቸው ጋራ በመወገን የኢትዩጵያን ጥቁር ሕዝብ የረጅም ዘመናት ነፃነትና ሥልጣኔ በመቃወም ተሞዳሙደዋል። ይልቁንም የጀርመን ንጉሥ ተብዬው ኢትዩጵያ በጣሊያን ሞግዚትነት ሥር ናትና አሜን ብላችሁ ተቀበሉ እያለ የዘላበደው ተመዝግቧል።

ከሁሉም በለይ ደግማዊ አጤ ምኒልክ ታመው ሳላ የጀርመን ሃኪም ተብዬ ሰላይ ሁሉ ሆን ብለው ክፍፍልና ብጥብጥ ፈጥረው ሕዝቡን ርስ በርስ ለማጋጨት ከፍተኛ ሴራ መፈጸማቸው ይታወቃል። በሳይናይድ የተመረዘ ሰው ወዲያው ይሞታል ዓመታት ታሞ አይቆይም። በሬው ላም ወለድ ወሬ አቀናብረው አጤ ምኒልክ በታማኝ ባለሟሎቻቸው ተመረዙ ብለው እንበለ እፍረት አናፍሰዋል።

ከታሪክ መዛግብት እንደምንረዳው ጀርመኖች በአፍሪቃ እንደ ፈረንሳይና እንግሊዝ ቅኝ ገዥነት ለማግኘት ቋምጠው ሲቅነዝነዙ የአፍሪቃን ቅርምት ጉባዔ በበርሊን ከተማ እ.አ 1884 አዘጋጅተዋል። በከፍተኛ የጥቁር ጥላቻና ንቀት በነጭ ዘር የበላይነት ትእቢት ተወጥረው በመዝመት በምሥራቅ አፍሪቃ ታንጋኒካ፣ ሩዋንዳ፣ ብሩንዲ እንዲሁም ናምቢያ ሐሬሮና ናማ ሕዝብ ወገኖቻችን ላይ የጀርመን ወራዳ ዘረኞች የፈጸሙት ኢሰባዊ ጭፍጨፋ ከቶ ምንግዜም አይረሳም።

በአድዋው ጦርነት ሶላቶውና ክልሱ ጣሊያን ድባቂ ሲመታ የጀርመን ትቢተኞች ዓይናቸውን በጨው አጥበው እንደ ተልባ ሲንጣጡ አልነበረም? ፈረንሳይ ለምን ለአበሻ ሕዝብ የጦር መሳሪያ ሸጠች ሩሲያም ለምን ረዳች እያሉ ተንደከደኩ። የኢትዩጵያ ጥቁር ሕዝብ የጣሊያን ሰላቶን ምንም ሳያስቀር በመመንጠሩ ነጭ ተብዬዎች ሁሉ ከአውሮፓ እስከ አሜሪካ በጣሊያን ሰላቶ ዘርያቸው መሸነፍ እርር ብግን ሲሊ በሌላው በኩል የጥቁር ሕዝብ ዘርያና ጭቁን ሕዝቦች ሁሉ በዓለም ዙሪያ በታላቅ ደስታ ተሞልተው የፀረ ቅኝግዛት የነፃነት ትግል ቀንዲል በያለበት አብርተዋል።

እነ፣
ፕሮፌስር ዶክተር አዩ ሞሚና
ዶክተር ገብሬ ጉልቱ፤ ዶክተር የውብ ዳር ዘለቀ፤ ዶክተር ገረመው ሰንጎሳ